የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ (ኢሕአፓ)

Ethiopian People's Revolutionary Party (EPRP)

## በ አውስትራለያ (ሜልበርን ከተማ) ስለተከሄደው ህዝባዊ ስብሰባ፤

## አጭር ዘገባ

**በሜልበርን ከተማ አውስትራሊያ የኢህአፓ ህዝባዊ ስብሰባ ተካሄደ።**

**በ4/9/11 ከቀኑ 2፡00 ሰዓት ከሰዓት በኋላ የኢህአፓ ደጋፊዎችና ጥሪውን አክብረው የተገኙ ሀገር ወዳድ ኢትዮጵያውያን የተገኙበት ይህ ስብሰባ፤ በትግሉ የተሰዉትን ሰማ ዕታት በማስታወስና የህሊና ፀሎት በመድረግ ተጀመረ። ከዚም ከኢህአፓ የበላይ አመራር አባልና የ አህጉራዊ አመራር ኮሚቴ ጓዶች በየተራ ፤ ስለወቅቱ የሀገራችን ተጨባጭ ሁኔታ ፣ ስለ ኢህአፓ ፖሊሲዎችና አቋሞች እንዲሁም በሀገር ቤትና በውጭ ድርጅቱ እያካሄደ ስላለው እንቅስቃሴ፤ ሰፊና ዝርዝር ማብራሪያ ከሰጡ በሁዋላ፣ ከተሰብሳቢ እንግዶች የቀረቡትን የተለያዩ ጥያቄዎችና አስተያየቶች በመቀበል፣ መልሶችና ማብራሪያዎችን ሰጥተዋል።**

**አብዛኛው ውይይትና ጥያቄዎች በግምባርና ትብብር ጉደዮች ላ ይ ያተኮረ ነበርናም ፤ በነዚህ ዓበይት ጉዳዮች ላይ የ ኢህአፓ አቋሞች ምን ምን እነደሆኑና ሲያደርጋቸው የቆየውንና አሁንም እያደረገ ያለውን እንቅስቃሴ በሰፊው በማብራራትና በመስረዳት ገላፃ ተደርጓል። ከዚህም በላይ በአሁኑ ወቅት ከወያኔው አሸባሪና አምባገነን አገዛዝ በተጨማሪ፣ የጠባብ ብሄርተኞች ና ደጋፊዎቻቸው በሀገራችን ህለውና ላይ ሊያስከትሉ የሚችሉትን አደጋ በመገንዘብ እያንዳንዱ ሀገር ዋዳድ ኢትዮጵያዊ ሁሉ ለሀገሩ በቁርጠኝነት ዘብ እንዲቆምና ከአንድነት ሀይሎች በተለይም ከኢህአፓ ጋር አብሮ በመሰለፍ፤ ያለማወላወል እነዲታገልና የዜግነት ግዴታውን እንዲወጣ በማሳሰብ ፣ ለሁሉም ሀገርዋዳድ ዜጋ ድርጅቱ ያቀረበውን ጥሪ በድጋሚ አስተላልፏል።**

**ሰብሰባውም በጥሩ መንፈስ ተካሂዶ ማምሻ ላይ ተጠናቅቋል።**

EPRP
P.O.Box 73337 Washington DC, 20056
USA

EPRP
BP 22
Bois Columbes 92270
France

Tel . 202-291-4217
Fax 202-291-7645
E-mail : ESPIC@aol.com
Website: http://www.EPRP.com